የዕጩ ምዝገባ መልመጃ፣ ሁኔታ **2**

ሁኔታ፣ በሶማሌ ክልል XYZ ለክልሉ ምክር ቤት የሚወዳደር አንድ ፖለቲካ ፓርቲ ዕጩ ABC የተባለ ፓርቲ ዕጩ በሆነ ሰው ላይ በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታ አቀረበ። በቅሬታዋ ላይ የ ABC ዕጩ አሁንም የጸጥታ መስሪያ ቤት ባልደረባ ሲሆን ከመንግስት ስራ አልለቀቀም በማለት ከሳለች። የ ABC ዕጩ በዕጩነት ከተመዘገበ እና የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ከጀመረ በኋላ ወደ ደህንነት ጽ/ቤት ሲገባ እና መኪናውም ጽ/ቤቱ ጋር መቆሟን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች አቅርባለች። የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታዋ በማስረጃ አልተደገፈም በማለት ውድቅ አድርጎባታል። የክልሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታዋን በፍትሐዊነት እንደማያይላት በማመን ቅሬታዋን በቀጥታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማቅረብ እና የ ABC ዕጩ በዕጩነት ለመቅረብ ያለውን ብቃት ለመሞገት ወሰነች።

ጥያቄ 1. ቅሬታውን ለመስማት ሥልጣን ያለው ማነው? የትኛው ፍርድ ቤት? (ወይም ሥልጣኑ አሁንም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ነው?)

ጥያቄ 2. ቅሬታ አቅራቢው መቼ እና የት ቅሬታውን ያቅርብ?

ጥያቄ 3. ጉዳዩ መቼ ውሳኔ ያግኝ?

ጥያቄ 4. ክሱን ለማስረዳት ምን አይነት ማስረጃ ሊቀርብ ይችላል?

ጥያቄ 5. ክሱ እውነት መሆኑ ቢረጋገጥ ምን አይነት ውሳኔ ወይም ቅጣት ይወሰናል?